# ለእራሱ ጉዳይ ያልሆነን፤ በጭራሽ በእኔ አላምነዉም!!

ከአዳም ጌታ (adamgeta89@yahoo.com)

12-21-14

ዉድ የዚች ጽሁፍ አንባቢዎች ጤናና ሰላም የዘወትር ሀብታችሁ እንዲሆን ከወዲሁ እየተመኘሁ ዛሬ ወደ እናንተ እንድትደርስ ብእሬን የሰበቅኩባት ከባህር ዳር ብሔራዊ ስታዲዬም በሙሉዓለም የባህል አዳርሽ አድርጎ ግዬን ሆቴል የሚደርሰዉ የ2.1 ኪ.ሜ መንገድ የማስፋ ስራን ተከትሎ በ10/04/2007 ዓ.ም በባህር ዳር ከተማ የተፈጠረዉን ረብሻ ምክንያት ላዉጋችሁ፡፡ የአማራ ክልል መዲና የጣና ዳር ፈርጧ ዉቧ ባህር ዳር ተፈጥሮ ከለገሰቻት በረከት ባሻገር አንድ ዉብ ከተማ ሊኖሯት የሚገቡ መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉላት በክልሉ መንግስት፣ በከተማዉ አስተዳደርና በህዝቡ በተቸራት ልዩ ትኩረት በለዉጥ ሂደት ጎዳና ላይ ትገኛለች፡፡



ሃገራችን የጀመረችዉ የህዳሴ ጉዞ በማሳካት የህዝባችን ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ መሰረተ ልማትን በማስፋፋት በርካታ ስራዎች እየተከናወኑ ነዉ፡፡ የመሰረተ ልማት ተቋማት በስፋትና በጥራት ባልተሟሉበት ሁኔታ የጀመርነዉ ፈጣን እድገት ዳር ማድረስ የሚታሰብ አይሆንም፡፡ ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆነች ከተማ እዉን ከማድረግ አኳያ ደረጃዉን የጠበቀ መንገድ ሚናዉ እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በመንገድ ዘርፍ ለተመዘገቡ ለዉጦች የመንግስታችን ቁርጠኝነትና የህዝባችን የተሟላ ተሳትፎ ደግሞ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መሬት ላይ የማስነካት ተጨባጭ ዉጤት በማስመዝገብ በኩል የተጫወቱት ድርሻ ተኪ

የለዉም፡፡ በዘርፉ በርካታ የተፈጠረዉ የስራ እድል፣ ለንግድ ቤቶች መስፋፋት የሚፈጥረዉ ምቹ ሁኔታ በአጠቃላይ መንገድ የሁልም ልማቶች ሞተር ሆኖ ከማገልገል አኳያ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡

ዉብና ለተስተናጋጅ ምቹ ሆቴሎች፣ ደረጃቸዉን የጠበቁ የስብሰባ አዳራሾች፣ ቁጥራቸዉ በየጊዜዉ እየጨመረ የመጡ ፋብሪካዎች፣ የመንገድ መሰረተ ልማት፣ ዓለም አቀፍ ደረጃዉን የጠበቀ ኤርፖርት...ምኑን ዘርዝሬ ምኑን ልተወዉ ብቻ እየሰፋችና እየለማች ያለች ከተማ ናት፡፡ በሁሉም የህይወት መስኮች ለዉጥን እያስተናገደች ያለችዉ ታዳጊዋ ከተማ በነዋሪዋ እንዲሁም በክልሉ ህዝብ ዘንድ እርካታ እየፈጠረና ተስፋን እያጫረ ጉዳይ ሆኗል፡፡ ለዉጡን ዳር ለማድረስ ሌት ተቀን የሚሰራዉ የክልሉ መንግስት፣ የከተማዉ አስተዳደርና ህብረተሰቡ የልማት እድገቱን አጠናክሮ ለማስቀጠልና የነገዋን የኢንዱስትሪ፣ የገበያና ምቹ የመኖሪያ ከተማ ባህር ዳርን በመሻት ዘርፈ ብዙ እቅዶችን አቅዶ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በያዝነዉ ዓመት የአማራ ብሄራዊ ክልል መዲና ዉቢቷ ባህር ዳር ደረጃቸዉን የጠበቁ መንገዶች ከ 600 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት ተመድቦላቸዉ እየተገነቡላት ትገኛለች፡፡ በህበረተሰቡ ተሳትፎ 30 በመቶ የወጭ መጋራትና በመንግስት ድጋፍ በተለያዩ የከተማዋ 46 አካባቢዎች 30 ኪ.ሜትር የሚሸፍን የኮብል ድንጋይ መንገድ ወጣቶች እያነጠፉ የከተማዋን ደረጃ ከፍ የሚያደርግ ስራ እየተሰራ ነዉ፡፡ በልማዳዊ አጠራር የኮበል ኢንዱስትሪ መንደር ተብሎ ከሚጠራዉ እስከ አየር ጤና በቅርቡ የተሰራዉ ደረጃዉን የጠበቀ አስፓልት መንገድ በመገንባቱ ህብረተሰቡን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከጎንደር ወደ ባህር ዳር የሚገባዉ መንገድ ስፋት ከከተማዋ እድገትና ከትራፊክ ፍሰቱ ጋር አብሮ የማይሄድ በመሆኑ የማስፋፊያ ፕሮጀክት ተቀርጾ ስራዉ እየተገባደደ ነዉ፡፡

ከአሮጌዉ ዲፖ በፈለገ ህይወት ሆስፒታል፣ በ ኤስ ኦ ኤስ ዞሮ በባታ ኮብል ድንጋይ መንገድ ወደ ኤርፖርት መንገድ የሚያደርስ፣ ከዋናዉ ንግድ ባንክ የባህር ዳር ሞጣ ደጀን መንገድን ተከትሎ የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የሚያስገነባዉ የሪፈራል

ሆስፒታል የሚያገናኝ ባለ ሁለት መንታ አስፓልት መንገድ፣ በአጠቃላይ ከ11.86 ኪ.ሜትር በላይ ደረጃዉን የጠበቀ መንገድ እንዲሰራ ዉል ተይዞ የቅድመ-ዝግጅት ስራዉ ተጠናቋል፡፡ ከሚሰሩት ሰፋፊ መንገዶች መሃሉ ላይ የሚኖረዉ የአረንጓዴ ቦታ እንዳለ ሆኖ በሁለቱም መንታ መንገዶች ዳር ሌላ የአረንጋዴ ስፍራ ቀጥሎ የእግረኛ መንገድ እንዲኖራቸዉ ዲዛይን የተደረጉ መንገዶች ከሌላዉ ልዩ ያደርጋቸዋል፡፡ አገልግሎት ከሚሰጡ ቀደምት ስራዎች መካከል የፖሊ ፔዳ መንገድ፣ የቀለበት መንገድና ከዲፖ ቀበሌ 14 የሚያገናኘዉ አስፓልት ከእግረኛ መንገድና መብራት ጋር የከተማችንን ደረጃ ከፍ ያደረጉ በመንገድ መሰረተ ልማት ዙሪያ የተከናወኑ አበይት ፍጻሜዎች ናቸዉ፡፡

የትራፊኩም ፍሰት ችግር ሳይገጥመዉ፣ የከተማዋን ዉበት እየጨመሩ፣ የህዝቡን እርካታ እያረጋገጡ ቀጣይ ለዉጡን ደግፎ ሌት ተቀን ከሚደክሙ የከተማችን ወጣት መካከል አንዱ ሆኜ አዎንታዊ ሚና ለመጫዎት መታደሌን ሳስብ ዛሬ ልንሰራዉ የሚገባንን ሰርቶ ለማለፍ በአገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ ከጓደኞቸ ጋር እተጋለሁ፡፡

የተሰሩና እየተሰሩ ያሉ መንገዶች እያስደሰቱኝ ጠባብ መንገዶች የሚሰፉበትን ጊዜ ስጠብቅ መልካም ዜና ሰማሁ፡፡ 700 ሚሊዮን ብር በሚጠጋ በክልሉ መንግስረት ወጪ ከተገነባዉ የባህር ዳር ብሄራዊ ስታዲየም በሙሉዓለም የባህል ማዕከል አድርጎ እስከ ግዮን ሆቴል የመንገድ ትራፊክ መብራት ድረስ ያለዉ ጠባብ መንገድን ባለ ሁለት መንታ ሆኖ ለእግረኛ፣ ለብስክሌትና ለመኪና ለየብቻ በሚያስተናግድ አግባብ ሊገነባ እንደሆነ ስሰማ እኔም እንደ ሌላዉ የባህር ዳር ህዝብ በደስታዉን ተጋራሁ፡፡ ይህ ጠባብ መንገድ ከመጥበቡ የተነሳ ስሚንቶ የጫኑ ጋሪዎች፣ እግረኛዉ፣ ባጃጅና መኪናዉ በአንድ ጊዜ የሚርመሰመስበትና እንደ ጠርሙስ አንገት የተጣበበ መንገድ መሆኑ በሄድኩበት ቁጥር የሚያሳስበኝና ለተደጋጋሚ የትራፊክ አደጋዎች የተጋለጠ ነዉ፡፡

ቀኑ 10/04/2007 ዓ.ም ነዉ፤ ዘወትር እንደማደርገዉ ጧት ተነስቼ የእለቱ ስራየን ለመከወን ጥድፍ ጥድፍ ስል አጀንዳቸዉ ምን እንደሆነ ያላወኩት የጥቂት ወጣቶች ስብስብ አገኙሁ፡፡ ምን እንደተፈጠረ ሁለት ወጣቶችን ጠጋ ብዬ ስጠይቅ " አልሰማህም እንዴ!? ከሁለት ቀን በፊት ወረቀት ተበትኗል እኮ " አሉኝ፤ እንዳልሰማሁ ስገልጽላቸዉ " የጥምቀት በዓል የሚከበርበት ቦታ ለኢንቨስተር ተሰጥቶ ልንቃወም ነዉ እዚህ የተገኘነዉ " አሉ፤ እንዴት ሊሆን ይችላል እያልኩ ወደ ሌላዉ ወጣት ተጠግቼ ስጠይቅ በጉዳዩ ግልጽ እንዳልሆንና የሚሆነዉን ለማየት እንደቆመ ነገረኝ ሌላዉ ደግሞ " አልሰማህም እንዴ የደመራ በአል የምናከብርበት ቦታ ላይ ያለዉ መስቀል ለልማት ተብሎ በቡልዶዘር ተነሳ እኮ " አለ፡፡ የመረጃዎች አለመመሳሰል እያስገረመኝ የሚሆነዉን ሁኔታ ለመከታተል ሞባይሌን አዉጥቸ ቢሮ ደዉዬ ቲኒሽ አርፍጄ እንደምገባ ገለጽኩ፡፡

አንድ የቅርብ ጓደኛዬን አግኝቸ የጊዩርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ለባለሃብት ተሰጠ እያሉ ያወራሉ ብሎ ነገረኝ፡፡ የበለጠ ሁኔታዉን ለማጥራት ቋመጥኩ፡፡ እኔ ያገኘኋቸዉን መረጃዎች ለጓደኛዬ እያጫወትኩት የተሰሩት አኩሪ የልማት ስራዎችን የሚያጥላሉ ጥቂት ከህዝብ ፍላጎት ዉጭ የተለየ ዓላማ ያላቸዉ ሃይሎች የፈጠሩት ዉዥንብር ነዉ ብለን ተስማማን፡፡

" ስራ የፈታ አዕምሮ የሰይጣን መስሪያ ቤት ይሆናል " እንዲሉ የፀረ-ህዝብ ሃይሎች የበሬ ወለደ ወሬ የጥምቀትና የመስቀል በዓል የሚከበርበት ቦታ ለኢንቨስትመንት ተሰጥቷልና ክርስቲያን የሆንክ ሁሉ ተነስተህ ተቃዎም  የሚል የሽብር ጥሪ ነዙ፡፡ ወጣቱ አቋሙን የማራመድ ከጥቃትም የመጠበቅ ህገ-መንግስታዊ መብት አለዉ፤ ጥያቄ ማንሳትም የሰለጠነ ህዝብ መገለጫና ይበል የሚያስብል ነዉ፡፡ ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ የመንግስት አካላት እንወያይ የምትፈልጉትን ጥያቄ ሁሉ አንሱና እንነጋገር የሚለዉን ዘመናዊ የችግር አፈታት መንገድ  እንቢኝ አሻፈረኝ፣ ሃብት ሳይወድም፣ ህይወት ሳይጠፋ፣ ልማት ሳይደናቀፍ በሚል በጣም የተሳሳተን የነዉጥ መንገድ መረጡ፡፡

መዳረሻዉን የክልሉ ምክር ቤት ያደረገዉ ይህ ህገ-ወጥ ሰልፍ ወደ ምክር ቤት እንገባለን! የሃይል እርምጃ ካልወሰድን አንቀመጥም! ሃይመኖታችን ተነክቷል ያለዉ ስርዓት አልባዉ ሰልፈኛ በክልል ምክር ቤቱ የጥበቃ ሰራተኞች ላይ ድንጋይ በመወርወር ህግን ተላለፈ፡፡ ብሎም ከጎንደር ወደ ባህር ዳር የሚመጣዉን የአባይን ድልድይ በመዝጋት የትራፊክ ፍሰቱን ገደበ፡፡

የክልሉ ምክር ቤት አዲስ ህንጻ 750 መቀመጫ ያለዉ የህዝብ ተመራጮች የመሰብሰቢያ አዳራሽ፣ ከ2 ሺ 500 ሰዎች በላይ የሚያስተናግድዉንና በዉስጡ የቀጥታ ስርጭት ስቱድዮ እንዲሁም በተለያዩ ቋንቋዎች የሚተረጎምበት የትርጉም ክፍል የያዘዉ በቅርቡ የአባይ ኮንቬንሽን ሴንተር ተብሎ የተሰየመዉ አዳራሽ፣ በአባይ ተፋሰስ ሃገሮች ስም የተሠየሙ መለስተኛ አዳራሾች የያዙ ሁለት ህንፃዎች ያሉበት በአጠቃላይ 500 ሚሊዬን ብር ወጪ ሆኖ የተገነባ ነዉ፡፡ ግቢዉ ዘመናዊ የደህንነት ካሜራዎች የተገጠሙለትና የአባይን ወንዝ ለሁለት ከፍሎ እንደገና እንዲገናኝ በማድረግ በተሰራ ሰዉ ሰራሽ ደሴት ላይ የተገነባ እጹብ ድንቅ የተባለለት ተፈጥሮንና ዘመኑ የደረሰበት የስነ-ህንጻ ጥበብ ተዋህዶ የተገለጸበት፣ ከተማዋን ግርማ ሞገስ ያላበሰ፣ ለአማራ ክልል ህዝቦች የታሪካቸዉና የባህላቸዉ የክብር ምንጭ የሆነ ተቋም ሲገነባ ምክር ቤቶች ለህዝብ ያላቸዉን የግልጸኝነት አሰራር ለማመላከት አጥር የሌለዉ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በአፍሪካ ህብርት፣ በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽንና በዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዓለማቀፍ ስብሰባዎችን እንደሚያስተናግድ ተመስክሮለት መሰል ስብሰባዎችን ማስተናገድ የጀመረ ትልቅ የከተማዋ ሃብትና የገጽታ መገንቢያ አዳርሻችን **ከመዝለሉ በፊት ምን እንደሆን ባላጣራዉ** ህገ-ወጥ ሰልፈኛ ተከቦ መስታዉቶቹ ላይ ጉዳት ለማድረስ ተሞከረ፡፡ ወደ ዉስጥም ዘልቀዉ በመግባት የአባይ ኮንቬንሽን አዳራሽ በሮችን ለመስበር ሞከሩ፡፡ ሁኔታዉን ለማርገብ በስፍራዉ ሲከላከሉ የነበሩ የፖሊስ አባላት ድንጋይ ተወረወረባቸዉ፡፡

በዚህ ያልተገታዉ የህገ-ወጦች ስብስብ በቅርቡ በ80 ሚሊዬን ብር የተገነባዉን የአማራ ብድርና ቁጠባ ህንጻን ላይ ተመሳሳይ ጥፋት ለመፈፀም ተሸጋገረ፡፡ የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ለ977 ሺ 183 ደንበኞቹ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከ23 ቢሊዬን ብር በላይ የብድር አገልግሎት በመስጠት የፀረ ድህነት ትግሉን እያፋጠነ ያለ የፋይናንስ ተቋም ነዉ፡፡ ከተበዳሪዎች መካከል ከ25-30 በመቶ የሚሆኑ የክልላችን ወጣቶችን ሆነዉ ሳለ በህገ-ወጦች ጥቃት ሲደርስበት ሳይ እራሱን የሚበላ ራዕይ አልባ ስብስብ መሆኑን ስታዘብ ይበልጥ አዘንኩ፡፡ 2 ሚሊዬን 6 መቶ ሺ ደንበኞች ያሉት አብቁተ 4.5 ቢሊዬን ብር ባላይ የክልሉ ህዝብ የቆጠበበት ከማንም በላይ ወጣቱንና ሴቶችን የሚያገለግል ተቋም ላይ ጥቃት ሲደርስ ከመመልከት በላይ ምን አሳፋሪ ነገር አለ!? በዉይይት መፍታት በሚቻልበት ሁኔታ በፀረ-ህዝብ ሃይሎችን የጥፋት ጥሪ በመደናገር ለጥፋት የተሰለፈዉ ሃይል በህዝቡና በፀጥታ ሃይሎች የተቀናጀ ጥረት ባይጨናገፍ ኖሮ በወቅቱ ካጋጠመዉ የአንድ ሰዉ የህይወት ህልፈት በላይ የከፋ ጉዳት ይደርስ ነበር፡፡

ከከተማዉ አስተዳደር የተሰጠዉን መግለጫ እንደተከታተልኩት ልማቱን በማስመልከት ከሃይማኖት አባቶችና ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር ዉይይት እንደተደረገበትና መንገዱ ሲሰፋ አራት ሜትር ብቻ ወደ መስቀል አደባባዩ የሚገባ እንጂ ለኢንቨስትመንት ቦታዉ እንዳልተሰጠ ተነገረ፡፡ እንዲሁም የሃይማኖት አባቶች ከከተማዉ አስተዳደር ጋር በ09/04/2007 ዓ.ም ተወያይተዉ ያመኑበትን በ12/04/2007 ዓ.ም (እሁድ) ከህዝበ ክርስቲያኑ ጋር ለመወያየት ቀጠሮ ተይዞ ባለበት፣ ዛሬም ነገም በማንኛዉም ጉዳይ መወያየት የሚቻልበት ምቹ ሁኔታና ተሞክሮ እያለን፣ ምንም አይነት የመንገድ ስራ ማሽኖች ወደ ስፍራዉ ዝር ባላሉበት ሁኔታ እንዴት የጥፋት ነጋሪት ይጎሰማል ጃል!? ለነገሩ ሰፊዉ ህዝብ የደገፈዉን ፀረ-ህዝብ ሃይሉ እንዴት ሊያደናቅፍ ይቻለዋል!?

የፍትህ ጥያቄ ማንሳት መቸም የማይቀር ክስተት ነዉ፡፡ አልተጠከምኩም በሚሉ ብዙ ድሆችና እላፊ እንጠቀም በሚሉ ጥቂቶች መካከል ፍልሚያ አለ፡፡ ድሉ የብዙሃን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ እንዲቋጭ መፍትሄዉ በልማት ማደግ ነዉ፡፡

ለዚህ ደግሞ በምክንያት ለመደገፍም ሆነ ለመቃዎም መረጃ የሰለጠነ፣ አንድ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማህበረሰብ በመገንባት ቁልፍ እንደሆነ ይታመናል፡፡

ዴሞክራሲ ተጀመረባት እንጂ ገና ባልዳበረባት ሀገር “ ሲሻኝ ጢስ ወጋኝ ” ብሎ አልቃሽ በበዛበት “ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ” እንዲሉ በዜጎች ህሌና የተዘራዉን የዴሞክራሲ ሲሳይ ማዕዱን እየደፉ ስቃይን ለወገን እየጋበዙ የት ሊደረስ!?

ስለ ሀገራችን መልካም ገጽታም ሆነ እግር ከወርች ጠፍሮ ስላሰራት ድህነት ስለሚባል ባላንጣ በድፍረት መጻፍ ያልቻለ፣ ቢያንስ ማንበብ ሲገባዉ በበጎ አሳቢዎች የተጻፈዉን መጽሃፍ ቀዳጅ የህዝብን ተቋማት ይንዳል፡፡ በፍኖተ ነፃነትና በግልጸኝነት መንፈስ በዜግነቱ እንዳይዝናና ያደገበትን ድብብቆስ እየተጫወተ እስከ መቼ?

ለነገረ በሃይማኖት ካባ ተሸፍኖ የሚራመድ የፖለቲካ ግብ ያለዉ አክራሪነት የዚህ ቀዉስ ጠንሳሽ እንደሆነ ድርጊቱ ይነግረናል፡፡ የኪራይ ሰብሳቢነት ዋሻ የሆነዉ አክራሪነት በሃይማኖት ሽፋን አጀንዳዉን ለማስፈፀም የተለያዩ የጥፋት ስልቶቹን እየነደፈ መልኩን በመቀያየር በህዝብ ላይ ከሚፈጽማቸዉ ደባዎች አንዱ ክስተት እንደሆነ በመገንዘብ ልማታችንን ከማንኛዉም ፀረ-ህዝብ ሃይሎች ጥቃት እንደንከላከል እንደ አንድ ሃላፊነት እንደሚሰማዉ የከተማዋ ወጣት መልዕክቴን እያስተላለፉኩ ህዝባዊና መንግስታዊ ተቋማትን የሚያፈርስ “ **ለራሱ ጉዳይ ያልሆነን ፣ በጭራሽ በእኔ አላምነዉም** ” በማለት በጀመርኩት አጀንዳ ላይ ያለኝ ትዝብት ቋጨሁ፡፡

**ቸር እንብት!!**